በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር

THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA MINISTRY OF FOREIGN AFFAIRS

ፕሬስ መግለጫ PRESSRELASE

# ኢትዮጵያና የተባበሩት አረብ ኤምሬቶች በንግድ እና ኢንቨስትመንት ለመተሳሰር ተስማሙ



የኢፌዴሪ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ዶ/ር ወርቅነህ ገበየሁ ከተባበሩት አረብ ኤምሬቶች የውጭ ግንኙነት እና ዓለም ዓቀፍ ትብብር ሚኒስትር ሼክ አብዱላሂ ቢን ዛይድ አል ናህያን ጋር በሁለቱ አገራት ግንኙነት ዙሪያ ተወያይተዋል።

ሁለቱ ሚኒስትሮች ባደረጉት ውይይት በኢትዮጵያና በተባበሩት አረብ ኤምሬቶች መካከል ብዙ ያልተነኩ የትብብር መስኮች እንዳሉ አመለከተው በሁለቱ አገራት መካከል ያለውን ግንኙነት በንግድ፣ ኢንቨስትመንት እና ቱሪዝም የበለጠ ለማጎልበት ከመግባባት ደርሰዋል።

ሁለቱ ሚኒስትሮች በአገሮቹ መሀከል ያለውን ግንኙነት ወደ ላቀ ደረጃ ለማሻገር ተስማምተዋል።

ዶ/ር ወርቅነህ ኢትዮጵያ ከተባበሩት አረብ ኤምሬቶች ጋር የላትን ግንኙነት ትኩረት እንደሚትሰጥ ገልፃዋል።

ሁለቱ ሚኒስትሮች ያለ ህጋዊ የመኖሪያና የስራ ፈቃድ በአገሪቱ የሚኖሩ ኢትዮጵዊን ዜጎች የሚሰሩበት ሁኔታ ዙሪያም ተወያይተዋል።

E-mail spokesperson@mfa.gov.et facebook @mfaEthspokesperson, Twitter @mfaEthspokesperson, YouTube https://www.youtube.com/channel/UCa_KUDpwCLMWyyQIjfilgZg ☎ 011-5-15 8928/011-5-53 6731 Fax 011-5-51-43-00 ✉393 Addis Ababa,Ethiopia

ዶ/ር ወርቅነህ በተባበሩት አረብ ኤምሬቶች ጉብኝታቸው ከአገሪቱ ሰራተኛና የሰው ሃብት ሚኒስትር መወያየታቸው ይታወሳል። እንዲሁም የተባበሩት አረብ ኤምሬቶች የሚገኘውን የኢፌዲሪ ኤምባሲን የስራ እንቅስቃሴ እና የዜጎች አገልግሎት አሰጣጥን ተመልክተዋል።

**የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር**

**ቃል አቀባይ ጽ/ቤት**

**ጥር 02 ቀን 2010 ዓ.ም.**